- “ልሞትላቸው ፈቃደኛ ነኝ” አለ።

- ኢየሱስ “በኀቼን ከኃጢአት ከሞትና ከሰይጣን ለማዳን ልሞትላቸው ፈቃደኛ ነኝ” አለ።

- ሌላስ ኢየሱስ ምን አል?

ዮሐንስ 14፡6

6- ኢየሱስ እንዲህ አለው “መንገዱ እኔ ነኝ፤ እውነትና ሕይወትም እኔው ነኝ በእኔ በኩል ካልሆነ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም።

- ኢየሱስ “እኔ ወደ እግዚአብሔር የማደርስ መንገድ ነኝ” አለ።

- ወደ እግዚአብሔር የሚያደርሰውን መንገድ ከፈለጋችሁ ወደ ኢየሱስ ተመለሱ።

- ኢየሱስ “እኔ እውነት ነኝ” አለ።
- እውነትን ለማወቅ ከፈለጋችሁ ወደ ኢየሱስ ተመለሱ።

- ኢየሱስ “እኔ ሕይወት ነኝ” አለ።
- የዘላለምን ሕይወት ከፈለጋችሁ ወደ ኢየሱስ ተመለሱ።

- በኢየሱስ አማካይነት ካልሆነ በቀር ማንም ወደ እግዚአብሔር አብ አይመጣም።



ትምህርት 60

1. ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን የጠየቃቸው ጥያቄ ምን ነበር?
ሀ- “ሰዎች እኔን ማን ይሉኛል” ብሎ ጠየቃቸው።

2. ደቀ መዛሙርቱ ምን ብለው መለሱለት?
ሀ- አንዳንድ ሰዎች ኢየሱስ መጥምቁ ዮሐንስ ነው ብለው ያስባሉ ሌሎች ኢየሱስ ኤልያስ ነው ብለው ያስባሉ። ሌሎች ኢየሱስ ከነቢያት አንዱ ከሞት ተነስቶ ነው ይላሉ አሉት።

3. ኢየሱስ መጥምቁ ዮሐንስ ኤልያስ ወይም ከነቢያት አንዱ ከሞት ተነስቶ ነው?
ሀ- አይደለም።

4. ቀጥሎስ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን ምን ጠየቃቸው?
ሀ- “እናንተሳ ማን ትሉኛላችሁ?” ብሎ ጠየቃቸው።

5. ጴጥሮስ ምን ብሎ መለሰለት?
ሀ- “አንተ ክርስቶስ ነህ” አለው።

6. እኛ ኢየሱስ አዳኝ አምላክ መሆኑን ካላመንን መዳን እንችላለን?
ሀ- አንችልም።

7. ኢየሱስ ወደፊት ስለሚሆኑት ነገሮች ለደቀ መዛሙርቱ ምን አስተማራቸው?
ሀ- የሕዝቡ መሪዎች እርሱን እንደሚገድሉት ነገር ግን በሶስተኛው ቀን እንደሚነሣ።

8. ኢየሱስ በተራራ ላይ ምን ሆነ?

ሀ- ኢየሱስ በጴጥሮስ በያዕቆብንና በዮሐንስ ፊት ተለወጠ።

9. ኢየሱስ ተለወጠ ማለት ምን ማለት ነው?

ሀ- በኢየሱስ ውስጥ ያለው መለኮታዊነት ወድ ውጭ አንጸባረቀ ማለት ነው።

10. ኤልያስ ማን ነበር?

ሀ- ኤልያስ ኢየሱስ ከመወለዱ በፊት በምድር ላይ ይኖር የነበረ የእግዚአብሔር ነቢይ ነው።

ለ- ከብዙ ዓመታት በፊት ኤልያስ ሳይሞት እግዚአብሔር ወደ ሰማይ ወሰደው።

11. ሙሴ ማን ነበር?

ሀ- ሙሴ እስራኤላውያንን ከግብጽ ምድር መርቶ ያወጣ ሰው ነበር።

ለ- ከብዙ ዓመታት በፊት ሙሴ ሞተ፤ እግዚአብሔር ሙሴን ወደ ሰማይ ወሰደው።

12. ኤልያስና ሙሴ ወደ ምድር የተመለሱት እንዴት ነበር?

ሀ- እግዚአብሔር አብ ኤልያስና ሙሴ ከኢየሱስ ጋር እንዲነጋገሩ ከሰማይ ወደ ምድር ላካቸው።

13. እግዚአብሔር ኤልያስና ሙሴ ከኢየሱስ ጋር እንዲነጋገሩ ለምን ፈለገ?

ሀ- ኢየሱስ ሊሞት ስለሆነ ኤልያስና ሙሴ እንዲያበረታቱት ስለፈለገ።

- ኢየሱስ በነበረበት ዘመን ብዙ አይሁዶች አረኞች ነበሩ።
- እረኞች ብዙ የበጎች መንጋ ይጠብቁ ነበር።



መጥቻለሁ።”

- ኢየሱስ “ሌባው የሚመጣው ሊሰርቅ ሊገድልና ሊያጠፋ ብቻ ነው” አለ።

- ሊሰርቅ ሊገድልና ሊያጠፋ ብቻ የሚመጣ ሌባ ማን ነው?
- ሰይጣን.

- ኢየሱስ ከሰማይ ለምን መጣ?
- ኢየሱስ ሕይወትን የዘላለምን ሕይወት ሊሰጠን መጣ።

- ኢየሱስና ሰይጣን የተለያዩ ናቸው።

- ሰይጣን ሰዎችን ሊሰርቅ ሊገድልና ሊያጠፋ መጣ።

- ኢየሱስ ለሰዎች ሕይወት ሊሰጥ መጣ።
- ሌላስ ኢየሱስ ምን አለ?

ዮሐንስ 10፡11

11- ኢየሱስ እንዲህ አለ “መልካም እረኛ እኔ ነኝ፤ መልካም እረኛ ሕይወቱን ስለ በጎቹ አሳልፎ ይሰጣል።”

- ኢየሱስ “መልካም እረኛ እኔ ነኝ” አለ።

- ኢየሱስ “በጎቼን በጣም ስለሚወድ ለእነርሱ ምን ላደርግላቸው ፈቃደኛ ነኝ” አለ?

- ይህ እውነት ነው?

- አይደለም ውሸት ነው።

- አንዳንድ ሰዎች "ወደ እግዚአብሔር የምንገባበት የቅድመ አያቶቻችን እምነት አለ" ይላሉ።

- ይህ እውነት ነው?

- አይደለም ይህም ደግሞ ውሸት ነው።

- ኢየሱስ እንድንበት ዘንድ የሚያስችል ብቸኛ በር እርሱ መሆኑን ተናገረ።

- በኖኅ ዘመን እግዚአብሔር ኖኅ ለመርከቡ ስንት በሮች እንዲሠራ አዘዘው?

- አንድ በር ብቻ።

- በኖኅ መርከብ አንድ በር መኖሩ ስለኢየሱስ ምን ያሳስበናል?

- የኖኅ መርከብ አንድ በር ብቻ እንደነበረው ሁሉ ወደ ዘላለም ሕይወት የሚያስገባው ብቸኛው በር ኢየሱስ መሆኑን ነው።

- በአንዱ በር ወደ ኖኅ መርከብ የገቡት ከሞት እንደዳነ ሁሉ በኢየሱስ የሚያምኑ ሁሉ ከሞት ይድናሉ።

- ሌላስ ኢየሱስ ምን አለ።

ዮሐንስ 10፥10ኣ

10- ኢየሱስ እንዲህ አለ "ሌባው ሊሰርቅ፥ ሊገድልና ሊያጠፋ ብቻ ይመጣል፤ እኔ ግን ሕይወት እንዲኖራቸውና እንዲትረፍረፍላቸው



-አብዛኛው የእስራኤል ምድር ደረቅ ስለሆነ እረኞች ለበጎቻቸው የግጦሽ ሣር ለማግኘት ብዙ ጊዜ ይቸገራሉ።

- ስለዚህ እረኞች ለበጎቻቸው ሁሉ በቂ የግጦሽ ሣር ለማግኘት እጅግ ርቀው ይጓዙ ነበር።

- እጅግ ርቀው ስለሚጓዙ እረኞች ከበጎቻቸው ጋር በሜዳ ላይ ያድሩ ነበር።

- በጎችን የሚሰርቁ ሌቦችና ነጣቂ አውሬዎች ስለነበሩ እርኞች ሌሊቱን በትጋት በጎቻቸውን ይጠብቁ ነበር።

- እረኞች በጎቻቸውን በሌሊት የሚጠብቁት እንዴት ነው?

- ከመምሸቱ በፊት የድንጋይ ካብ ወይም የእሾህ አጥር ሰርተው አንድ በር ያደርጉ ነበር።

- ካቡ ተሰርቶ ሲያልቅ እረኛው በጎቹን በካቡ ውስጥ አስገብቶ መግቢያ በር ላይ ይተኛል።

- እረኛው መግቢያ በር ላይ ይተኛል።

- እረኛው መግቢያ በር ላይ የሚተኛው ለምንድን ነው?

- በካቡ ውስጥ ያሉትን በጎች ለመከላከል።

- እረኛው በካቡ በር ስለተኛ ልክ እንደካቡ መዝግያ ነበር።

- በቅድሚያ እረኛውን ሳያገኙ ሌቦችም ሆነ አውሬዎች በጎቹ ወዳሉበት መግባት አይችሉም።

- አንድ ቀን ኢየሱስ ምሳሌ በመጠቀም ስለራሱ ሕዝቡን አስተማረ።

ዮሐንስ 10:7

7-ስለዚህ ኢየሱስ ደግሞ እንዲህ አላቸው፤ “እውነት እላችኋለሁ፤ የበጎች በር እኔ ነኝ።”

- ኢየሱስ “እኔ የበጎች በር ነኝ” ሲል ምን ማለቱ ነው?
- ኢየሱስ እርሱ ከሞት የምንድንበት መንገድ መሆኑን መናገሩ ነው።

- እረኛ በጎቹን ከሞት የሚያድን በር እንደሆን ሁሉ ኢየሱስም እኛን ከሞት የሚያድነን በር ነው።

- ሌቦች ከካቡ ውጭ በጎቹን ለመስረቅ እንደሚጠባበቁ ሁሉ ሰይጣንና አጋንንቱም ሰዎችን ሁሉ ለመስረቅ ይጠባበቃል።

- አውሬዎች ከካቡ ውጭ ሆነው በጎቹን ለመብላት እንደሚጠባበቅ ሁሉ ኃጢአትና ሞትም ሰዎችን ሁሉ ሊበሉ ይጠባበቃሉ።

- እንደ ሌባ ሰይጣን ቅድመ አያትቻችሁን ለብዙ ዓመታት ስርቋቸዋል።

- ሰይጣን ሰዎችን የሚሰርቀው ለማጥፋት ነው።
- እረኞች በጎቻቸውን እንደሚወዱ ሁሉ ኢየሱስም በጎቹን ይወዳል።

- የኢየሱስ በጎች እነማን ናቸው?

- ኃጢአታቸው ሞት እንደሚያመጣባቸው የሚያውቁና ከኃጢአታቸው እንዲያድናቸው ኢየሱስን የሚጠሩት ናቸው።



- ኢየሱስ ከኃጢአትና ከሞት ከሞት ሊያድነን ይፈልጋል።

- ኢየሱስ ከሰይጣንና ከአጋንንቱ ሊያድነነ ይፈልጋል።
- ኢየሱስ ሌላ ምን አለ።

ዮሐንስ 10፡8

8- ኢየሱስ እንዲህለል “ከእኔ በፊት የመጡት ሁሉ ሌቦችና ቀማኞች ነበሩ በጎቹ ግን አልሰሟቸውም።”

- ኢየሱስ ከመወለዱ በፊት ሌሎች ሰዎች ወደ አይሁዶች መጥተው “አዳኝ ነን” ብለዋል።

- ኢየሱስ “እነዚህ ሰዎች ሌቦችና ወንበዴዎች ናቸው” ብለዋል።
- ኢየሱስ ሌላ ምን አለ።

ዮሐንስ 10፡9

9- ኢየሱስ እንዲህ አለ “በሩ እኔ ነኝ፤በእኔ በኩል የሚገባ ሁሉ ይድናል፤ ይገባል፤ይወጣል፤ መሰማሪያም ያገኛል።

- ኢየሱስ በእርሱ አማካይነት የምንድንብት ብቸኛ በር እርሱ መሆኑን ተናገረ።

- በካቡ መካከል አንድ በር ብቻ እንዳለ ሁሉ ኢየሱስ ወደ ዘላለም ሕይወት የሚያስገባ ብቸኛ በር ነው።

- አንዳንድ ሰዎች “ወደ እግዚአብሔር የሚያስገቡ ብዙ በሮች አሉ” ይላሉ።